# የነቢዩ
# የዮሴፍ ስሚዝ
# ምስክርነት

የኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ
ክርስቶስ ቤተክርስቲያን



# የነቢዩ የዮሴፍ ስሚዝ
# ምስክርነት

በኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተ ክርስቲያን የታተመ ሶልት ሌክ
ሲቲ ዩታ፤ ዩ ኤስ ኤ።

የማሳተም መብት 1988
የኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ
ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንት
ኮርፓሬሽን በዩናይትድ ስቴትስ በአሜሪካ
ታተመ።
Revised 1990

The Prophet Joseph Smith's
Testimony in Amharic
32667 506

# የነቢዩ የዮሴፍ ስሚዝ ምስክርነት

የሚቀጥለው ዘገባ ዮሴፍ ስሚዝ የፃፈው ታሪክ አካል ነው። የኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሲመሠረት ስለደረሱ ዋና ዋና ሁኔቶች ይናገራል።

ታህሣሥ 23 ቀን 1805 ዓ.ም. በሻሮን ከተማ በዊንድዘር ወረዳ በሸርሞንት ስቴት ተወለድሁ። አባቴ ዘጠኝ ዓመት ሲሆነኝ ከሸርሞንት ስቴት ተነስቶ በኒው ዮርክ ስቴት ወደ ምትገኝ ፓልሚራ ወደምትባል ከተማ ሄደ። ከዝያም ከአራት አመት በኋላ አባቴ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ወደማንቼስተር ከተማ ሄደ።

ወደማንቼስተር ከሄድን ከአንድ ዓመት በኋላ አዚያ ያልተለመደ የሃይማኖት መነሳሳት ተጀመረ።

በሜሰዲስት ቤተክርስቲያን ተጀምሮ፡ የቀጣናውን ቤተክርስቲያናት ሁሉ አቀፈ። ብዙ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን መጡ። የነርሱም መምጣት በሰዎች መካከል ብዙ መነሳሳትና ክርክር ፈጠረ። አንዳንዶች ውነትን የያዝነው እኛ ብቻ ነን አሉ። ሌሎች የሜሰዲስት ቤተክርስ ቲያንን ደገፉ። አንዳንዶች ለፕሬስቢይተሪያን ቤተክርስቲያን ሲከራከሩ ሌሎች ለባፕቲስት ቤተክርስቲያን ይከራከሩ ነበር።

የተለያዩ የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን ሁሉ ለመለወጥ በርትተው ሠሩ። መለወጥ የሚባለውን ቃል መጠቀም ይወዱ ነበር። ሰዎች የቤተክርስቲያን አባል እስከሆኑ ድረስ የየትኛውም ቤተክርስቲያን አባል ቢሆኑ ግድ የለም ይሉ ነበር።

ተለውጠው የቤተክርስቲያን አባላት የሆኑት ሰዎች ለሰዎች ያላቸውን ፍቅር ይገልፁ ነበር። የተለያዩ ቤተክርስቲያናት አባላት ከሆኑ በኋላ ግን ቄሶችም ሆኑ የተለ ወጡ ሰዎች ለሰዎች ያላቸው ፍቅር የእውነት አልነበረም። ብዙ ሰዎች ከተለወጡ በኋላ ክፉና የተምታታ ስሜት ተሰማቸው።

የአንዱ ቤተክርስቲያን ቄሶችና የተለወጡ ሰዎች ከሌላ ቤተክርስቲያን ቄሶችና ከተለ ወጡ ሰዎች ጋር ይከራከሩ ነበር። ቀደም ሲል ሰዎች ለሌሎች ሰዎች የነበራቸው ፍቅር በክርክር ምክንያት ጠፋባቸው።

በዚያን ጊዜ 14 ዓመቴ ነበር። ከቤተ ሰባችን አባሎች በከፊል የፕሬስቢይቴሪያን ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ይፈልጉ ነበር። እነርሱም እናቴ ሉሲ፤ ወንድሞቼ ሃይሩን፣ ሳሙኤል፣ ሃሪሰንና እንዲሁም እህቴ ሰፍሮኒያ ነበሩ።

ይህ መነሳሳት እየቀጠለ ሄደ። እኔም ችግር ገጠመኝ። ስለሃይማኖት አጥብቄ አሰ ብሁ። ምንም እንኳን ጠንከራ ሰሜት ቢኖረኝም የየትኛውም ቤተክርስቲያን አባል አልሆንሁም። ይሁን እንጂ በተቻለ መጠን ዘውትር በተለያዩ ስብሰባዎች እገኝ ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሜሰዲስት ቤተክር ስቲያን አባል ለመሆን መረጥሁ። አባል የመ ሆን ሰሜትም ተሰማኝ። በተለያዮ ቤተክርስቲ ያኖች መካከል ብዙ ክርክርና የሃሳብ መምታት ሰለነበረ እንደእኔ ላለ ወጣትና ልማድ ላላከበተ ሰው የትኛው ቤተክርስቲያን እውነተኛ ወይም ሰህተኛ እንደሆነ በእርግጥ የማውቅበት መንገድ አልነበረም።

የተለያዮ ክርክሮችና ሃሳቦች ሰለነበሩ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አስብ ነበር። የትኛው ቤተክርስቲያን ትክክለኛ ይሆን? ወይስ ሁሉም ስህተት ይሆኑ ይሆን? እያልሁ አስብ ነበር። አንዱ ትክክል ቢሆን እንኳን እንዴት ለማወቅ እችላለሁ? እያልሁ አስብ ነበር።

የተለያዩ የሃይማኖት አስተማሪዎች የነእርሱ ቤተክርስቲያን እውነተኛ ስለመሆኑ የሚያቀርቡዋቸው ምክንያቶች በጣም አደናግረውኝ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን የያቆብ መልዕክት ምዕራፍ 1 ቁጥር 5ን አነብ ነበር። "ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድ ለው፡ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፡ ለእርሱም ይሰጠ ዋል። " የሚል ነበር።

ይህ የመፀሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማንንም ከሚመስጥ በላይ እኔን መሰጠኝ። ወደልቤ በታላቅ ሃይልና ስሜት የሚገባ መሰለ ደግሜ ደጋግሜ አሰብኩበት። የማደረገው ጠፍቶኝ ስለነበረ የማንንም ያህል ከእግዚ አብሔር ጥበብ እንደሚያስፈልገኝ አውቅነበር። ይበልጥ ጥበብ ካላገኘሁ በስተቀር ማድረግ ያለብኝን ነገር ለማወቅ እንደማልችል አውቅ ነበር። የተለያዩ የቤተክርስቲያን አስተማሪዎች የመፀሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች በተለያየ መንገድ ስለሚገነዘቡ መፀሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ መልስ ለማግኘት አይቻ ልም ነበር።

## የዮሴፍ መጀመሪያ ራዕይ

ያዕቆብ እንዳመለከተው እግዚአብሔርን ካልጠየቅሁ በስተቀር ተደናግሬ እንደምቀር ገባኝ። እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወሰንሁ። ጥበብ ለሚጐድላቸው ጥበብ የሚሰጥና ስለጠየቁም የማይቆጣ ከሆነ እኔም ልጠይቅ እንደምችል አሰብሁ።

እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ቆርጬ ፀሎት ለማድረግ ጫካ ውስጥ ገባሁ። ጊዜው 1820 ግም የፀሐያማ ወራት ነበር። በጧት ተነሰቸ ለመጸለይ ወደ ጫላ ውሰጥ ገባሁ ከዝያም ጫህጠየ ሰይልይ በህይወቴ ውሰጥ የመጀመርያ ጌዜ ነበር።

ቀደም ብዬ ወደመረጥሁት ሥፍራ ከደረስሁ በኋላ ብቻዬን መሆኔን ለማረጋገጥ ዙሪያውን ተመለከትሁ። ከዚያም በኋላ በጉልበቴ ተንበርክኬ የልቤን ምኞት ለእግዚ አብሔር መግለፅ ጀመርሁ። ወዲያውኑ በአ ንድ በሚያሸንፈኝ ሃይል ተያዝሁ። በሚያስገ ረም አኳኋን እንዳልናገር ምላሴን አሰረው። ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ዙሪያዬን ከበበኝ። ለአ ንድ አፍታ የምጠፋ መሰለኝ። ስለሃይሉ አልገመትሁም። ማንም የማይሰተከከለው ነበር። ከዚህ በፊት ይህ ሀይል? ከቶ አልተሰ ማኝም።

"እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ቁርጥ
ውሳኔ አድርጌ ወደጫካ
ውስጥ ሄድሁ። "



ያለኝን ጉልበት ሁሉ አሰባስቤ ከያዘኝ የጠላት ኃይል እንዲያድነኝ ወደ እግዚአብ ሔር ፀለይሁ። ተስፋ መቁረጥ ስጀምርና እራሴን ለጥፋት አሳልፌ ለመስጠት ሳዘጋጅ ከፀሐይ የደመቀ የብርሃን አምድ ከራሴ አየሁ። በቀስታ ወደኔ ወረደና በራሴ ላይ አበራ።

ብርሃኑ እንደታየ ይዞኝ ከነበረው ሃይል ነፃ ሆንሁ። ብርሃኑ በኔ ላይ ባበራ ጊዜ ሁለት ክብራቸውንና ብርሃናቸውን ለመግለፅ የሚሳነኝ ሰዎች ታዩኝ። ከኔ በላይ በአየር ላይ ቁመው ነበር። አንዱ በስሜ እየጠራ አናገ ረኝ። ሌላውን እያመለከተም እንዲህ አለ "ይህ የምወደው ልጄ ነው። እርሱን ስማው። "

ለመናገር በቻልሁ ጊዜ ከኔ በላይ ቁመው የነበሩትን ሰዎች የየትኛው ቤተክርስቲያን አባል መሆን እንደሚገባኝ ጠየቅሁ።

ሁሉም ስህተት ስለሆኑ የየትኛውም ቤተክርስቲያን አባል እንዳልሆን ተነገረኝ። እኔን ያነጋገረኝ ሰው ኬሎች እምነታቸው ሁሉ በእርሱ ዘንድ አስፀያፊ እንደሆነ ነገረኝ ።

ሰባኪዎቹ ሁሉ የተበላሹ ናቸው አለ። በቃል እንደሚያከብሩት ከልባቸው ግን እንዳልሆነ ተናገረ። የሰዎችን ትዕዛዝ እንደእ ግዚአብሔር ትምህርት እንደሚያስተምሩ ነገረኝ። ትዕዛዞቹ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ቢመስሉም ሰባኪዎች የእግዚአብሔርን እውነተኛ ሃይል እንደሚክዱ ተናገረ።

የየትኛውንም ቤተክርስቲያን አባል እንዳልሆን ነገረኝ። በአሁኑ ጊዜ ልጽፋቸው የማልችል ብዙ ነገሮች ነገረኝ። ራዕይ በተ ፈፀመ ጊዜ ዳንሁ። በጀርባዬ ተኝቼ ወደሰማይ አመለከት ነበር።

ራዕይ ካየሁ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከአንድ ከሜሰዲስት ቤተክርስቲያን አገልጋይ ጋር ባጋጣሚ ተገናኘን። ቀደም ሲል በጠቀ ስኩት የሃይማኖት መነሳሳት ውስጥ በንቃት ይሳተፍ ነበር። ከእርሱ ጋር ስለሃይማኖት

"የብርሃን አምድ ልክ ከራሴ በላይ አየሁ። "



በመነጋገር ላይ ሳለን ስላየሁት ራዕይ ነገርሁት። በእሱም መልስ በጣም ተደነቅሁ።

የነገርሁትን ነገር ክብደት አልሰጠውም። ስለነገርሁት ነገር ንቀት ነበረው። ያየውም ራዕይ ከዲያብሎስ ነው። በአሁኑ ጊዜ ራዕይ የሚባል ነገር የለም። የዚህ ዓይነት ነገሮች በክርስቶስ ሐዋርያት ዘመን የተፈፀሙ ሰለሆነ በአሁኑ ጊዜ ከቶ አይደገሙም አለ።

የራዕዩን ታሪክ በመናገሬ ብዙ ሰዎች ስለኔ የተዛባ አስተሳሰብ እንዳላቸው በቶሎ አወቅሁ። በፅኑ አሳደዱኝ። ማሳደዱም እያደገ ሄደ። የታወቅሁ ሰው አልነበርሁም። በ14እና በ15 ዓመት ዕድሜ መካከል ያለሁ ልጅ ነበርሁ። ከፍተኛ ሥራ አልነበረኝም። ይሁን እንጂ ታዋቂ ሰዎች እኔን እንደትልቅ ሰው በመቁጠር ህዝብን በኔ ላይ በማነሳሳት ያሳድዱኝ ነበር። ቤተክርስቲያኖች ሁሉ እኔን ለማሳደድ ተባበሩ።

እኔ ከ14 ዓመት በላይ ነበርሁ። የዕለት ጉርሴን ለማግኘት ሁልቀን መሥራት ነበረብኝ። ስለዚህም የታወቁ የቤተክርስቲያን ሰዎች ሁሉ ስለኔ መቸገር ለምን እንዳ ስፈለጋቸው ያኔ ይገርመኝ ነበር። አሁንም ይገርመኛል። እኔ ትልቅ ሰው እንደሆንሁ ለምን እንዳሰቡና ለምን እንዳሳደዱኝ ስለኔ መጥፎ ነገር ለምን እንዳሉ ደግሞ ይገርመኝ ነበር። ነገሩ እንግዳ ቢመስለኝም እውነታው ይኸው ነበር። ሰለዚህም በጣም አዝን ነበር።

ይሁን እንጂ በሁለት ህልዋን መጉብኘቴ ደግሞ እውነት ነበር። እኔም በንጉሡ በአግሪፓ ፊት እንደተከራከረ እንደሐዋርያው ጳውሎስ እንደሆንሁ አስብ ነበር። እርሱም ስለራዕይ፣ ስላየው ብርሃንና ስለሰማው ድምፅ ተናገረ። ሌሎች ሰዎች ግን እርሱ ያበደ ነው በማለት ያፌዙበት ነበር። ይሁን እንጂ ያ ራዕይ የማየቱን ዕውነታ አልለወጠውም።

በእውነትም ራዕይ አየ። ማየቱን ያውቅ ነበር። ምንም ያህል ስደት ዕውነታውን ሊለውጠው አይችልም ነበር። ይህን በማለቱ

ቢገድሉት እንኳን ራዕይ ማየቱን ያውቅ ነበር። ቢሞትም ራዕይ ማየቱን ያናገረው ድምፅ መስማቱን እያወቀ ይሞት ነበር። በዓለም ያሉ ስዎች ሁሉ ራዕይ እንዳላየ ሊያሳምኑት ወይም ሊያሳስቡት አይችሉም ነበር።

የኔ ሁኔታ ከእርሱ ሁኔታ ጋር ተመሳ ሳይ ነበር። ብርሃን አይቼ ነበር። በብርሃኑ መካከል ሁለት ህልዋንን አየሁ። በዕውነት ተናግረውኛል። ራዕይ አየሁ ስላልሁ ብጠላም ወይም ብስደድም ማየቴ እውነት ነበር። ራዕይ አየሁ ስላልሁ ሰዎች አሳደዱኝ። ሰለኔም ብዙ ውሸት ተናገሩ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ሰዎች እውነትን ስለተናገርሁ ለምን እንደሰደዱኝ ይገርመኝ ነበር። እኔ ማነኝ እግዚ አብሔርን የምቋቋም? ያየሁትን ነገር እንድክድ ለማድረግ ሰዎች ለምን ፈለጉ? ራዕይ አይቻለሁ። ራዕይ ማየቴን አውቃለሁ። ራዕይ ማየቴን እግዚአብሔር እንደሚያውቅ አውቅ ነበር። ልክደው አልችልም። ልክድም አልደፍርም። ይህንን ብክድ እግዚአብሔርን እንደማስቀይምና እንደሚፈርድብኝ አውቅ ነበር።

በዚያን ጊዜ በዓለም ውሰጥ ስላሉ ቤተክርስቲያኖች የነበረኝ አስተሳሰብ ያጠግ በኝ ነበር። የማንኛቸውም አባል መሆን እንደሌለብኝ አውቅ ነበር። እግዚአብሔር ተጨማሪ መመሪያ እስኪሰጠኝ ድረስ እንደነበርሁ መቀጠል ነበረብኝ። የያዕቆብ ቃሎች እውነት እንደሆኑ አወቅሁ። ጥበብ የሚጐድለው ሰው እግዚአብሔርን ሊጠይቅ እንደሚችልና ጥበብ እንደሚቀበል አወቅሁ። እግዚአብሔርም እንደ ማይቆጣ ተረዳሁ።

## የሞሮናይ ጉብኝት

የዕለት ሕይወቴን በዚህ ዓይነት እስከ መሰከረም 21ቀን 1823 ዓ·ም·ቀጠልሁ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ራዕይ አየሁ ስላልሁ ሃይማ ኖተኞችና ኢሃይማኖተኞች በፅኑ ያሳድዱኝ ነበር።

ራዕይ ባየሁበት ጊዜና በ1823 መካ ከል ብዙ ዓይነት ስደት ደረሰብኝ። በነዚህ ዓመታት እኔም ለጋኔን ተከፊ ነበርኩ። የማንኛውም ቤተክርስቲያን አባል እንዳልሆን ተከልክዬ ነበር። ወዳጆቼ መሆን በሚገባቸ ውና በደግ ሊቀበሉኝ በሚችሉ ወዳጆቼ ተሰደድሁ።

የተታለልሁ ከመሰላቸው በአግባቡና በፍቅር ከስህተቴ ሊመልሱኝ ይገባ ነበር። እኔ ግን ከብዙ ዓይነት ሰዎች ጋር በመቀላቀል ብዙ ስህተቶችን ሠራሁ። የወጣትነትና የሰው ባህርይ የሚያስከትላቸውን ስህተቶች ሠራሁ። እነዚህም ስህተቶች እግዚአብሔርን ወደሚያ ስቀይሙ ወደ ብዙ ፈተናዎች መሩኝ። ይህም በመሆኑ አዝናለሁ። ይህንን ስናገር ማንም ከባድ ኃጢአት የሠራሁ እንዳይመስለው። ከባድ ኋጢአት የመሥራት ዝንባሌ ከቶ አልነበረኝም።

በነዚህም ምክኒያት ስለድክመቴና ስለጉድለቴ ፀፀት ይሰማኛል። መስከረም 21 ቀን ማታ ከተኛሁ በኋላ ሁሉን ቻይ እግዚአ ብሔር ኃጥያቶቼንና ደካማ ሥራዎቼን ሁሉ ይቅር እንዲለኝ ፀለይሁ። ስለኔ ያለውን ሰሜት አውቅ ዘንድ እንደገና እንዲታየኝ ፀለይሁ። ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ እራሱን እንደ ሚያሳየኝ ሙሉ እምነት ነበረኝ።

እየፀለይሁ ሳለሁ በመኝታ ቤቴ ብርሃን ታየኝ። ብርሃኑ እየጨመረ ሄደ። የዕኩል ቀን ብርሃን አከለ። ወዳያውኑ ክቡር ህልው ከአል ጋዬ አጠገብ። በአየር ላይ ቁሞ ነበር። እግሩ መሬት አልነካም።

ያሸበረቀ ነጭ ካባ ለብሶ ነበር። ከም ድራዊ ነገሮች ሁሉ የነፃ ነበር። እንደዚያ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም። ምንም ነገር በምድር ላይ እንደዝያ ይነጣል ብዬ አላምንም ነበር። እጆቹና እግሮቹ አልተሸፈኑም ነበር። እግሮቹ ከተረከዙ ጥቂት ከፍ ብሎ አልተሸ ፈኑም። እራሱና አንገቱም ግልጥ ነበር።

"ሞሮናይ የተባለ ክቡር ሰው ከአልጋዬ አጠገብ ተገልጾ እግዚአብሔር ለኔ ሥራ እንዳለው ነገረኝ።"



ከካባው በስተቀር ሌላ ልብስ
አልለበሰም። ክፍት ስለነበረ ደረቱን ለማየት
እችል ነበር።

ልብሱ ብቻ አልነበረም በጣም ነጭ
የነበረው። እርሱም ለመግለፅ ከሚቻል በላይ
ብርሃን ና መብረቅ ይመስል ነበር። ክፍሉም
ብርሃን ነበር ይሁን እንጂ ከእርሱ አካባቢ
ብርሃን አልነበረውም። መጀመሪያ ላየው
ፈራሁ። ግን ወዲያው ፍርሃቴ ተወኝ።

በስሜ ጠርቶ ስሙ ሞሮናይ እንደሆነ
ነገረኝ። የእግዚአብሔር መልዕክተኛ እንደሆነና
እግዚአብሔር ለኔ ሥራ እንዳለው ነገረኝ።
ወደፊት የሁሉም ብሔር ህዝቦች ጐሳዎችን
ቋንቋዎች ስሜን እንደሚያውቁ ነገረኝ።
አንዳንዶች ስለኔ በጐ ነገር ሲናገሩ ሌሎች
ስለኔ ውሸት እንደሚናገሩ ነገረኝ። በሌላ
አነጋገር በሰዎች ሁሉ ዘንድ አንዳንዶች ጥሩ
ሰው መሆኔን ሲያስቡ ሌሎች አመፀኛ እንደ
ሆንሁ ያስባሉ ማለት ነው።

በወርቅ ሰሌዳ የተፃፈና የተቀበረ መጽ
ሐፍ እንዳለው ነገረኝ። መጽሐፉ ጥንት
በአሜሪካ አህጉር ይኖሩ ስለነበሩ ሰዎች
ይተርካል። ደግሞ በመጽሐፉም ውስጥ ጌታ
ለጥንት ሰዎች የሰጣቸው ወንጌልእንዳለ።
ከሰሌዶቹም ጋር ሁለት ድንጋዮችእንደተቀበሩ
ተናገረ። እነዚህ ድንጋዮች በብዕር ማዕቀፍ
የተዘጋጁ ሆነው ከደረት ጋር የተያየዙ
ነበሩ። ኡሪምና ቱሚም ተብ ለው ይጠሩ
ነበር።

በጥንት ዘመን እነዚህ ድንጋዮች ያሉ
ትና ሊጠቀምባቸው የሚችል ሰው ነቢይ
ይባል ነበር። ድንጋዮቹ መጽሐፉን ለመተር
ጐም እግዚአብሔር ያዘጋጃቸው ነበሩ።

እነዚህን ነገሮች ከነገረኝ በኋላ ከብ
ሉይ ኪዳን ትንቢቶችን መጥቀስ ጀመረ።
መጀመሪያ የጠቀሰው የሚልኪያስ መጽሐፍ
የምዕራፍ ሶስት ክፍል ነበር። በዚያው
መጽሐፍ አራተኛውን ምዕራፍ ጠቀሰ። ከኛ
መጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት የተለየ ነበር። የመጀ
መሪያውን ጥቅስ እንደምናነበው በመጥቀስ
ፈንታ እንደሚከተለው ጠቀሰው። "በእውነት

ቀን ይመጣል እንደጋመ እሳት የሚያቃጥል። የሚኮሩና አመፀኞች ሁሉ እንደገለባ ይነዳሉ። አለየሠራዊት ጌታ እግዚአከሔር የሚመጡት ሥርና ቅርን ጫፍ እንዳይኖራቸው ያቃጥሉዋቸዋል።"

አምስተኛውን ጥቅስ እንደሚከተለው ጠቀሰ። "እነሆ ጌታ የሚመጣበት ትልቁና አስፈሪ ቀን ከመድረሱ በፊት በነቢዩ በኤል ያስ አማካይነት ክህነትን እገልጽልሃለሁ" አለ።

ስድስኛውንም ጥቅስ በተለየ መንገድ ጠቀሰው። "በልጆቹ አዕምሮ ውስጥ እግዚ አብሔር ለወላጆቻቸው የሰጠውን ተስፋ ስለኖረ የልጆቹ ልብ ወደጥንት አባቶቻቸው ይመለሳል። ይህ ባይሆን ጌታ ሲመለስ ምድር ባዶ በሆነች ነበር።"

በተጨማሪ ኢሳያስ ምዕራፍ አሥራ አንድን ጠቀሶ በዚህ ምዕራፍ የተነገሩት ትንቢቶች ሊፈፀሙ ተቃርበዋል አለ። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሶስት ከቁጥር 22-23 ያለውን በሐዲስ ኪዳን በትክክል እንደተጻፈው ጠቀሰ። በዚህ ምዕራፍ የተጠ ቀሰው ነቢይ ክርስቶስ እንደሆነ ተናገረ። ነገር ግን የእርሱን ድምፅ የማይሰሙ ሰዎች ከእርሱ ሰዎች የሚለዩበት ቀን እንዳልመጣ ወደፊት ግን እንደሚመጣ ተናገረ።

የኢዮኤልን ሁለተኛ ምዕራፍ ከቁጥር 28-32 ድረስ ያለውን ጠቀሰ። ይህ ትንቢት እንዳልተፈፀመ በቅርቡ ግን እንደሚፈፀም ተናገረ። ለአህዛብ ወንጌልን የመቀበል ዕድል የሚሰጥበት ጊዜ በቅርቡ እንደሚጀመር ተና ገረ። ከመፀሐፍ ቅዱስ ብዙ ጥቅሶችን ጠቅሶ ብዙ ማብራሪያዎችን ሰጥቷል። እነዚህን እዚህ መጻፍ አልችልም።

ሰሌዶቹን ለኔ የሚሰጥበት ጊዜ ገና እንዳልደረሰ ነገረኝ። ጊዜው ሲደርስና ሲሰጠኝ ለማንም እንዳላሳይ አስጠነቀቀኝ። ካሳየሁ ግን እንደሚጠፋ ነገረኝ። እግዚአብሔር እንዳሳያቸው ለነገረኝ ብቻ አሳያለሁ። እርሱ ስለሰሌዳዎች እያነጋገረኝ ራዕይ አየሁ።

በዓይነ ህሊናዬ ሰሌዶቹ የተቀበሩበትን

ቦታ ለማየት አችል ነበር። ራዕይ ግልፅና ጉልህ ስለነበረ ወደሥፍራው በሄድሁ ጊዜ ቦታውን አወቅሁት።

እነዚህን ነገሮች ከነገረኝ በኋላ በክፍሉ የነበረው ብርሃን በሰውነቱ ዙሪያ ሲሰበሰብ አየሁ። እርሱ ከቆመበት ሥፍራ በስተቀር የክፍሉ ብርሃን ተሰብስቦ ክፍሉ ጨለማ ነበር። ወዲያው የብርሃን ቀስት የመሰለ ነገር ወደ ሰማይ ሲዘረጋ አየሁ። በብርሃኑ ቀስት ወደሰማይ ሄዶ ተሰወረ። ከዚያ በኋላ ክፍሉ እንደቀድሞው ጨለማ ሆነ።

ስለ ገጠመኝ ተኘቼ አስብ ጀመር። ይህ ሰማያዊ መልዕክተኛ ስለነገረኝ ነገር አገረምና አደነቅ ጀመር። እያሰብሁ ሳለሁ ክፍሌ እንደገና በብርሃን ሲሞላ አየሁ። ከመቅፅበት ሰማያዊው መልዕክተኛ ከአልጋዬ አጠገብ ቆመ። መጀመሪያ የነገረኝን ነገር እንዳለ ደግሞ ነገረኝ። ቀደም ሲል ከተናገረው ምንም አላዛነፈም። ከዚያ በኋላ በምድር ላይ ሰለሚመጣ ፍርድና አስከፊ ውጤቶቹ ነገረኝ። በረሃብ በጦርነትና በመቅሰፍት ሰው እንደሚጠፉ ነገረኝ።

በምድር ላይ እነዚህ ፍርዶች በዚህ ትውልድ ላይ እንደሚፈፀሙ ተናገረ። ይህንን ካለ በኋላ ወደሰማይ ሄደ።

ከዚህ በኋላ ነገሩ በአዕምሮዬ በጣም ስለተቀረጸ መተኛት ተሳነኝ። ባየሁትና በሰማሁት ተመስጬ ተኛሁ። ያው መልዕ ክተኛ በአልጋዬ አጠገብ እንደገና ሲቆም በጣም ተደነቅሁ። ቀደም ሲል የነገረኝን ነገር ለሶስተኛ ጊዜ ነገረኝ። ቤተሰቤ ድሃ ስለሆኑ ቅጠሎችን ሽጬ ሃብታም እንድሆን ሰይጣን እንደሚፈትነኝ አስጠነቀቀኝ።

ይህንን እንዳላደርግ ካስጠነቀቀኝ በኋላ ቅጠሎቹን የማገኝበት ዋናው ምክኒያት የእግ ዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት እንደሆነ ነገረኝ። በሌላ በምንም ፍላጐት ተፅዕኖ እንዳ ያድርብኝ ነገረኝ። ለሌላ ምክኒያት ቅጠሎችን ማግኘት እንዳማይቻል ተናገረ።

ለሶስተኛው ጊዜ መልዕክቱ እንደበፊቱ ወደ ሰማይ ተመለሰ። ባለፈው ሁኔታ ለብቻዬ

አሰብሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መለዕኩ እንደሄደ የዶሮ ጩኸት ተሰማ።

ከአጭር ጊዜ በኋላ ከአልጋዬ ተነስቼ ወደሥራ ሄድሁ። እንደሌላው ቀን ሁሉ መሥራት ጀመርሁ። ነገር ግን በጣም ደክሞኝ ስለነበረ ምንም መሥራት አቃተኝ። በአጠገቤ ይሠራ የነበረው አባቴ ሁኔታዬን አይቶ ወደቤት እንድሄድ ነገረኝ። ወደቤት መሄድ ጀመርሁ። ነገር ግን እንሠራበት የነበረውን መስከፐአጥር ማለፍ አቃተኝ። ጉልበቴ ሁሉ ዛላ። ወደመሬት ወደቅሁ። ለተወሰነ ጊዜ አዕምሮዬን ሳትሁ።

መጀመርያ የማስታውሰው በስሜ እየ ጠራ ያነጋገረኝን ድምፅ ነበር። ቀና ብዬ ስመ ለከት ያው መልዐክተኛ እንደበፊቱ በብርሃን ተከቦ በአጠገቤ ቁሞ አየሁት። ማታ የነገረኝን ነገር ደገመልኝ። ያየሁትን ራዕይና የተቀበል ኩትን ትዕዛዝ ሄጄ ለአባቴ እንድነግረው አዘዘኝ።

ታዘዝኩት። ወደአ ባቴ ተመልሼ ስለራዕይ ነገርኩት። እርሱም ሲመልስ ይህ ከእግዚአብሔር ነው አለ። ሂድና የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ያዘዘህን ነገር አድረግ አለኝ።

መስኩን ትቼ የእግዚአብሔር መልዕ ክተኛ ሰሌዶቹ ተቀብረዋል ወዳለኝ ሥፍራ ሄድሁ። ያየሁት ራዕይ ግልፅ ስለነበረ ከሥፍ ራው ስደርስ አወቅሁት።

## የወርቅ ሰሌዶች

በኒው ዮርክ ውስጥ በማንቼስተር መንደር አጠገብ ከአካባቢው ሁሉ ከፍተኛ የሆነ ኮረከታ አለ። ሰሌዶች በዚህ ኮረከታ ውስጥ ከምዕራብ በኩል ኮረብታው ጫፍ ላይ በድንጋይ ሳጥን ውስጥ ነበሩ። ጫፎቹ ቀጠን ብለው ከመሬት ውስጥ ሲሆኑ መሃሉ ከመሬት በላይ ይታይ ነበር።

በጫፉ ዙሪያ የነበረውን አፈር ካነሳሁ በኋላ ብትር አግኝቼ ከሥር ሰካሁት። የሳጥኑን ውስጥ ስመለከት ሰሌዶቹን አየሁ። መልዕክ ተኛው እንዳለው ኡሪም ቱሚምና የደረት ሰሌዳውን አየሁ። የነበሩበት ሳጥን ከድንጋይ የተሠራ ሆኖ በሲሚንቶ የተለሰነ ነበር። ከሳ ጥኑ መጨረሻ ሁለት ድንጋዮች ወደ ጐን ተቋራጭ ሆነው ተሠርተው ነበር። በነዚህ ሁለት ድንጋዮች ላይ ሰሌዶቹና ሌሎችም ዕቃዎች ነበሩ።

ሰሌዶቹን ለማውጣት ሞከርሁ። ነገር ግን መልዕክተኛው ከለከለኝ። እነርሱን ለመው ሰድ ጊዜው እንዳልሆነና ጊዜውም ከአራት ዓመት በፊት እንደማይሆን ነገረኝ። ልክ ከአንድ ዓመት በኋላ እዚያው ቦታ እንድመ ጣና እዚያ እንደሚያገኘኝ ነገረኝ። ሰሌዶቹን እስክቀበል ድረስ በያመቱ ወደዚያው መሄድ እንደሚገባኝ ነገረኝ።

ልክ እርሱ እንዳዘዘኝ በያመቱ ወደዚ እሄድ ነበር። ያንኑ መልዕክተኛ አያገኘሁ ትምህርትና ዕውቀት ይሰጠኝ ነበር።

በነዚህ ጊዜዎች ጌታ ምን እንደሚያደ ርግና የእርሱ መንግስት እንዴት መመራት እንዳለበት እንደሚፈልግ ነገረኝ።

አባቴ በጣም ድሃ ሰለነበረ እንደቀን ሠራተኛ መሥራት ነበረብን። ዕድል ባጋጠመን ቁጥር ሁሉ በቀን ወይም ለበለጠ ጊዜ እራሳ ችንን እናከራይ ነበር። አንዳንዴ ሥራችን ቤታችን አጠገብ ስለሚሆን ቤት እንኖር ነበር። ሌላ ጊዜ ከቤት ርቀን እየሰራን እንድንኖር እንገደድ ነበር። ሳናቋርጥ በመ ሥራት መጠነኛ ኑሮ እንኖር ነበር።

በጥቅምት ወር 1825 ዓ·ም· በኒው ዮርክ ውስጥ ቼናንጎ ወረዳ ይኖር በነበረ ጆዛያ ሰቶአል በተባለ ሽማግሌ ሰው ተቀጠርሁ። እርሱ ዘንድ በተቀጠርሁበት ጊዜ ሃርሞኒ በተባለ ከተማ ውስጥ ከሚኖር ይሳሃቅ ሄል ከተባለ ሰው ጋር እንድኖርና እንድበላ ቀጣሪዬ አደረገ። እዚያ ኤማ ሄል የተባለች ውንና ኋላ ሚስቴ የሆነችውን የሰውየውን የበኩር ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ አየሁ። ለአቶ

"በመጨረሻም ሰሌዳቹን የምቀበልበት
ጊዜ ደረሰ።"



ሳሎአን በመሥራት ላይ እያለሁ ታህሣሥ 18 ቀን 1827 ዓ·ም· ተጋባን።

ካገባሁ በኋላ ወዲያው ለአቶ ስቶአል መሥራት ትቼ ወደአባቴ ቤት ተመልሼ አባቴን በእርሻ ረዳሁት።

በመጨረሻም ሰሌዳውን ኡሪምና ቱሚ ምን እንዲሁም የደረት ሰሌዳውን የምቀበል በት ጊዜ ደረሰ። መስከረም 22 ቀን 1827 ዓ·ም·ሌላ ዓመት አለፈ።

እንደተለመደው ሰሌዶቹ ወደተቀበሩበት ቦታ ሄድሁ። ያው መልዕክተኛ ሰሌዶቹን ሰጠኝ። ለሰሌዶቹ ሃላፊ መሆኔን ነገረኝ። በቸልተኝነት ወይም በዝንጉነት ምክኒያት ቢጠፉ ከጌታ እንደምቋረጥ ነገረኝ። መልዕ ክተኛው ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ባቆያቸው ግን እንደሚጠበቁ ነገረኝ።


መልዕክተኛው ሰሌዶቹን በጥንቅቃ እን ዳቆይ ለምን እንደነገረኝና ተመልሼ መጥቼ አወስዳቸዋለሁ ለምን እንዳለ ወዲያው ተረ ዳሁ። ሰሌዶቹ እንዳሉኝ ሰዎች እንዳወቁ ከኔ ለመውሰድ ጥረት አደረጉ። ለማሰብ የሚቻለ ውን ሁሉ አደረጉ። ማሳደዱም ከቀድሞው የከፋ ሆነ።

ቢቻላቸው ብዙ ሰዎች ሊሰርቁኝ ፈለጉ። እግዚአብሔር በጥበቡ ሰሌዶቹ ከኔ ጋር በደህና እንዲቆዮ አደረገ። ማድረግ ያለብኝን ነገር ካደረሁ በኋላ መልዕክተኛው ሊወስዳቸው መጣ።

እርሱ መልሼ ሰጠሁት። ይህችን ጽሑፍ እስከምጽፍለት እስከ ግንቦት 2 1838 ዓ·ም·ድረስ በእርሱ ጥበቃ ሥር ናቸው። ሰሌዶቹ ከተመለሱ በኋላም ስደቱ ቀጠለ። ስለ እኔና ስለአባቴ ቤተሰብ ሺህ ወሬዎች ተነዙ። ከተነዙት ወሬዎች አንድ ሺህኛውን ብጽፍ ብዙ መጻሐፎች ይወጣው ነበር። ስደቱ በጣም ስለከፋ ማንቼስተርን መተው ነበረብኝ። ሚስ ቴና እኔ በፔንስልቫኒያ ውስጥ ሱስኩዊሃና ወደ ተባለ ወረዳ ሄድን።

በዚህ ጊዜ እኔና ባለቤቴ በጣም ድሆች ነበርን። በስደቱ ምክኒያት ከድህነት የምንላቀ ቅበት አዝማሚያ አልነበረም። በችግራችን

"ከሰሌዳዎች ላይ ጽሑፎችን መገልበጥ ጀመርሁ።"



ውስጥ ማይክል ሃሪስ የተባለ ሰው እውነተኛ ወዳጅ ሆነን። እርሱም በኒው ዮርክ ውስጥ በዌን ወረዳ በፓልሚራ ከተማ የሚኖር የተከበረ ገበሬ ነበር። ወደኛ መጥቶ ለጉዞአችን የሚሆን ሃምሳ ብር ሰጠን። በወቅቱ በደረሰን እርዳታ ምክኒያት ፔንስልቫኒያ ለመድረስ ቻልን። እዚህ እንደደረስን በሰሌዳው የነበሩትን ጽሑፎች በወረቀት መገልበጥ ጀመርሁ።

ብዙ ጽሑፎችን ገለበጥሁ። በኡሪምና በቱሚም አማካይነት እንዳንዶቹን ተረጐምሁ። ይህንንም ያደረሁት በታህሣሥ ወር እማቴ ቤት ከደረስሁ ጊዜ ጀምሮ እስከወዲያኛው ጥር ወር ድረስ ነበር።

በየካቲት ወር ከላይ ስሙን ጠቅሼ የነበረው አቶ ሃሪስ እኛ ወዳለንበት መጣ። ከሰሌዳው ላይ የገለበጥኳቸውን ጽሑፎች ሰጥቼው ወደኒው ዮርክ ይዟቸው ሄደ። በእርሱና በጽሑፎቹ ላይ ስለደረሰው ነገር ቀጥሎ ተጽፈዋል። ከተመለሰ በኋላ ልክ እርሱ እንደነገረኝ ጽፌዋለሁ።

"ወደኒው ዮርክ ከተማ ሄጄ ጽሑፎቹ ንና ትርጉማቸውን ለኘሮፌሰር ቻርልስ አንቶን አሳየሁት። ኘሮፌሰር አንቶን በድርሰት ችሎታው የታወቀ ሰው ነበር። ትርጉሙ ትክክል እንደሆነ ነገረኝ። ከዚህ ቀደም ከግብፅ ቋንቋ ከተተረጐሙት ሁሉይህ ትክክለኛ መሆኑን ነገረኝ።

"ከዚያም ያልተተረጐሙትን ጽሑፎች አሳየሁት። እርሱም ትክክለኛ የግብፅ፤ የቻልዲክ፤ የአሲሪያን የአረብ ጽሑፎች መሆናቸውን ነገረኝ። ትክክለኛ ጽሑፎች መሆናቸውንና በትክክል መተርጐማቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ለፓልሚራ ሰዎች ሰጠኝ።

"ደብዳቤውን በኪሴ አድርጌ ከቤት መውጣት ስጀምር ጠራኝ። ጽሑፎቹ የሚገኙበትን የወርቅ ሰሌዳ ወጣቱ ልጅ እንዴት አገኘ ሲል ጠየቀኝ። የእግዚአብሔር መልአክ የነበሩበትን ቦታ አሳየው አልኩት።

"ከዚያም የጻፈውን ደብዳቤ እንደገና

ለማየት ጠየቀኝ። ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት። ደብዳቤውን ወሰዶ ቀዳደደው። መላዕክት በአሁኑ ጊዜ ሰውን አይጐበኙም አለኝ። ሰሌዳዎቹን ወደእርሱ ባመጣቸው እንደሚተ ረጉማቸው ነገረኝ። ከሰሌዳዎቹ በከፊል የተ ቆለፉ ስለሆነ ላመጣቸው አልተፈቀደልኝም አልሁ።

"የተቆለፈ መጽሐፍ ለማንበብ እንደማ ይችል መለሰልኝ። ትቼው ወደ ዶክተር ሚቼል ሄድሁ። እርሱም ፕሮፌሰር አንቶን ስለፅሑፎ ቹና ስለትርጉማቸው ያለውን አፀደቀ።"

የማርቲን ሃሪስ ሪፖርት አበቃ። በሚያ ዝያ 5 ቀን 1829 ዓ·ም·ኦሊቨር ካውድሪ ወደኔ ቤት መጣ። ከዚያ በፊት አይቼው አላውቅም። አባቴ በሚኖርበት መንደር እንደሚያስተምር ነገረኝ። አባቴ ልጆች ስለነበሩት አቶ ካውደሪከ አባቴ ቤት ለጥቂት ጊዜ ቆይቶ ነበር። ቤተሰቤ ሰሌዳዎቹን እንዴት እንዳገኘሁ ነግረውት ሰለ ሰኤደዎች ሊያነጋግረኝ መጣ።

ሚያዝያ 7 ቀን አቶ ካውድሪ ወደኔ በመጣ በሁለተኛ ቀን የሞርሞንን መጽሐፍ በእርሱ ፀሐፊነት መተርጐም ጀመርሁ።

## ክህነት ተመለሰ

እስከ ግንቦት 1829 ዓ·ም·ድረስ መተርጐም ቀጠልን። ከሰሌዳዎቹ ስለጥምቀትና ስለኃጢአት ስርዬት የሚያወራውን በከፊል አይተናል።

በዚያው ወር አንድ ቀን ለመፀለይና እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ ጫካ ሄድን። በመፀለይና ጌታን በመጥራት ላይ እያለን ከሰማይ መልዕክተኛ በደመና ብርሃን መጣ። እጆቹን በራሳችን ላይ አኑሮ እንዲህ እያለ አፀናን።

በመሲሁ ስም የአሮናዊ ክህነት ለሁለታ ችሁም እንደኔ አገልጋይ ለሆናችሁት እሰጣ

"በግንቦት 15 ቀን 1829 ዓ.ም.
መጥምቁ ዮሐንስ የአሮናዊ ክህነት ለዮሴፍ
ስሚዝና ለኦሊቨር ካውድሪ ሰጠ።"



ለሁ። ይህ ክህነት የጥብኝት፤ የመልዕክት ማስተማር፤ ንሰሐ መግባት፤ ሰለኃጢያት ሰርየጉ የመስጠም ጥምቀት ቁልፍ ይይዛል አለ። የሌዊ ልጆች የጽድቅ መሰዋዕት ለጌታ ያቀርቡ ዘንድ ክህነት ከምድር ከቶ አይወሰድም አለ።

መልዕክተኛው የአሮናዊ ክህነት በስዎች ላይ እጃችን የማኖርና የቅዱስ መንፈስ ስጦታ የመስጠት ስልጣን እንደማይሰጠን ግን ይህ ሥልጣን ቆይቶ እንደሚሰጠን ነገረን። ሄደን አንዱ ሌላውን እንድናጠምቅ አዘዘን። እኔ ኦሊቨር ካውደሪን እንዳጠምቅ እርሱ ደግሞ እኔን እንዲያጠምቅ አዘዘን።

የጉበኘንና የአሮናዊ ክህነት የሰጠን ሰው ስም ዮሐንስ ነበር። ይህም በአዲስ ኪዳን ዮሐንስ መጥምቁ ይባል የነበረው ሰው ነው።

ያደረገውን ነገር እንዲያደርግ ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ እንዳዘዙት ተናገረ። እነርሱ የመልከጼዴቅ ክህነት ቁልፍ ይዘዋል። ይህም ክህነት ወቅቱ ሲደርስ እንደሚሰጠን ነገረን። በዚያን ጊዜ እኔ የቤተክርስቲያኑ የመጀመ ሪያው ካህን ካውደሪ ደግሞ ሁለተኛው ካህን ተብለን እንደምንጠራ ተናገረ።

ከዚህ በኋላ እርሰበእርሰችን ተጠማመቅን። ኦሊቨርን መጀመሪያ አጠመቅኩት። ከዚያ በኋላ እርሱ አጠመቀኝ። በታዘዝነው መሠረት እጄን በራሱ ላይ በማኖር የአሮናዊ ክህነት ሰጠሁት። እርሱም እንዲሁ በማድረግ የአሮ ናዊ ክህነት ሰጠኝ።

እያንዳንዳችን ከሙሉ መጥለቅ ጥምቀት ከወጣን በኋላ ከሰማያዊ አባት ክቡር በረከ ቶችን ተቀበልን። ኦሊቨር ካውድሪን እንደጠ መቅኩት ቅዱስ መንፈስ እርሱ ላይ መጣ። ተነስቶም ወደፊት የሚሆኑ ብዙ ሆኔቶችን ተናገረ። እንዲሁም እኔን እንደጠመቀኝ ተነስቼ ስለወደፊት ቤተክርስቲያን መመሥረትና ስለቤተክስቲያኑና ስለዘመኑም ሰዎች ብዙ ነግሮችን ተናገርሁ።

በመልዕክተኛው ግንቦት 15 ቀን 1829 ዓ·ም· ፀናን ተጠመቅንም። በቅዱስ መንፈስም

ተሞልተን እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ስላቀደ ተደሰትን።

መንፈስ ቅዱስ ይገባን ዘንድ አዕምሮአ ችን አበራልን። የመፀሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እውነተኛ መልዕክትና ዓላማ ድሮ ልናስብ ከምንችለው በላይ ይበልጥ እንድንገነዝብ አደረገ። በአካባቢው ይደርስብን በነበረ ስደት ምክኒያት ክህነት መቀበላችንን ሚስጢር አድርገን ያዝን።

በተጨማሪም ሃይማነተኞች ሰዋች በየጊዜው በኛ ላይ ሰዎች በማስነሳት አሰፈራሩን። ነገር ግን የአማቴ ቤተሰቦች በመከላከላቸው የእግዚአከሔር መሳርያወች ነበሩ። አማቴና ቤተሰቡ ሁኩተኞችን ይቃወሙ ነበር። እኔን ይወዱኝ ስለነበረ የትርጉም ሥራዬን ያለማቋረጥ እንድሠራ ሌሎች እንዲተዉኝ ይፈልጉ ነበር። እኛን ከህገ ወጥ ድርጊት አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ለመከላከል ቃል ገብተው ነበር።

እየተረጎምን ሳለ ጌታ ሶስት ልዩ ልዩ ምስክሮችን የምተረጉምበትን ሰሌዳ እንዲያዩ እንደሚልክ ተማርን። እነዚህ ምስክሮች ሰሌ ዳዎችን እንዳዩ የሚመሰክሩ ነበሩ። (የሞርሞን መጸሐፍ የተባለው ትርጉም እራሱ በእስቴር 5 2-4 እና ኒፋይ 27 12 ስለዚሁ ይናገራል)

ይህንን ከተማረን በኋላ ኦሊቨር ካውድ ሪ፤ ዳዊት ዊትመርና ማርቲን ሃሪስ ሶስቱ ልዩ ምስክሮች ሊሆኑ ይችሉ እንደሆነ ጌታን እንድ ጠይቅ ተመስጠው ጠየቁኝ። ጌታን ጠየቅሁ እርሱም ሶስቱ ልዩ ምስክሮች እነርሱ እንደሆኑ ገለፀልኝ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ማርቲን ሃሪስ፣ ዳዊት ዊትመር፣ኦሊቨር ካውድሪና እኔ ሆነን ወደጫካ ሄድን። ጌታ ቃል በገባው መሠረት ሰሌዳዎቹን እንዲያዩ ከልብና በትህትና ወደ ጌታ ለመፀለይ አሰብን። ለዚህም ዳዊት ዊት መር ቤት አጠገብ ያለውን ጫካ መረጥን። እዚያም ሄደን ተንበርክከን መፀለይ ጀመ ርን። ሃያል ጌታ የገባውን ቃል እንደሚፈፀም እምነት ነበረን።

እኔ መጀመሪያ እንድፀልይና ሌሎችም በተራ ጮክ ብለው እንዲፀልዩ ወሰን። መጀመሪያ ለሰማያዊ አባታችን በፀለይን ጊዜ መልስ አላገኘንም። ከእግዚአብሔር ምልክት አልነበረም። አሁንም በየተራ ወደ እግዚአ ብሔር ፀለይን። መልሱ እንደበፊቱ ነበር።

ለሁለተኛ ጊዜ መልስ ስናጣ ማርቲን ሃሪስ መልስ ያላገኘነው በርእሱ ምክኒያት እንደሆነ አሰበ። ከኛ መለየት እንዳለበት አሰበ። እርሱ ከሄደ በኋላ ተንበርክከን ፀለይን። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከኛ በላይ አየር ላይ ብረሃን አየን። ወዲያው መልዐክ ሰሌዳቹን ይዞ ከፊታችን ቆመ።

በላያቸው የተቀረፁትን ጽሑፎች እናይ ዘንድ ሰሌዳቹን አንድ በአንድ አገላብጦ አሳየን። ወደ ዳዊት ዊትመር ዞሮ ዳዊት፤ ጌታ የተባረከ ነው። የእርሱንም ትእዛዝ የሚጠብቅ የተባረከ ነው አለ።

ወዲያው ከዚያ በኋላ ከኛ በላይ ከነበ ረው ብርሃን ድምፅ ሰማን። እንዲህ አለ "እነዚህ ሰሌዶች በእግዚአብሔር ሃይል የተገለፁ ናቸው። በእግዚአብሔር ሃይልም ተተረጐሙ። ያያችሁትም ትርጉም ትክክል ነው። አሁን ሰለምትሰሙት ነገር እንድት መሰክሩ አዝዣችኋለሁ። "

ከዚያም በኋላ ዳዊትንና ኦሊቨርን ትቼ ማርቲን ሃሪሰን ፍለጋ ሄድሁ። ከሩቅ ቦታ ላይ ከልብ ሲፀልይ አገኘሁት። እርሱም ጌታ መልስ እንዳልሰጠው ወዲያው ነገረኝ። ሌሎቻችን የተቀበልነውን በረከት እርሱም ይቀበል ዘንድ አብረን እንድንፀልይ ጠየቀኝ። አብረን ፀለይን ለፀሎታችን መልስ አገኘን።

ከመጨረሳችን በፊት ተመሳሳይ ራዕይ አየን። ቀደም ሲል የሰማሁትን ነገር ሰማን። በዚህ ጊዜ ማርቲን በታላቅ ደስታ ጮኸ። "በቃ። በቃ። አይቻለሁ። አይቻለሁ። " አለ። ወደላይ ዘለለና "ሆሣዕና፤ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን" ሲል ጮኸ። እነዚህ ሶስት ሰዎች ክቡር ራዕይ በእግዚአብሔር ምህረት ያዩ ስለሆነ የታዘዙትን ነገር ማለትም ሰሌዶ ችን ማየታቸውን ለዓለም መመስከር ነበረ

ባቸው። ይህንንም ለማድረግ የሚከተለውን ጻፉ፤

## የሶስቱ ሰዎች ምሥክርነት

ይህንን መጽሐፍ ለምታዩ ለዓለም ብሔር ሕዝቦች፣ጐሳዋችና ሁሉ በእግዚ አብሔር አብና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ አማካይነት የመጽሐፉ ትርጉም የተመሠረተ ባቸውን ሰሌዶች አየን እንላለን። ሰሌዶቹ የኒፋይ ህዝቦችን፣የወንድሞቻችን፣የላማን ሕዝቦችን፣እንዲሁም ከግብጽ የመጡትን የጃ ረድ ህዝቦችን ታሪክ ይዘዋል።

በሰሌዶቹ ላይ የነበሩትን ጽሑፎች በአብ ስጦታና ሃይል እንደተተረጐሙ እናውቃለን። የጌታ ድምፅ ገልጾልናል ይህ መጽሐፍ እውነት እንደሆነ እናውቃለን። በሰሌዶቹ ላይ የተቀ ረጹት ጽሑፎች በእግዚአብሔር ሃይል እንጂ በሰው ሃይል እንዳልሆነ እንመሰክራለን።


የእግዚአብሔር መልዐክ ከሰማይ ወርዶ ሰሌዶቹን እንዳሳየን በፅሞና እንገልጻለን። በሰ ሌዶቹ ላይ ተቀርፀው የነበሩት ጽሑፍች በዓ ይናችን አይተናል። በእግዚአብሔር አብና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ እነዚህን ነገሮች አይተናል። እውነት መሆናቸውን እንመሰክ ራለን። አስደናቂ ነው እንላለን። የጌታ ድምፅ ስለዚህ እንድንመሰክር ያዘዘን ስለሆነ እንመ ሰክራለን።

የክርስቶስ ታማኝ ብንሆን ያለኀጢአት እንደምንኖር ክርስቶስ ሲፋርደን ኀጢአት እንደ ማይገኝብንና ከእርሱም ጋር ለዘላለም በመንግሥተ ሰማይ እንደምንኖር እናውቃለን። ለዚህ ሁሉ ነገር ክብር ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እንሰጣለን። አሜን።

ኦሊቨር ካውድሪ
ዴይቪድ ውትመር
ማርቲን ሃሪስ

እነዚህ ሁኔቶች ከሆኑ በኋላ የሚከተለው ምስክርነት ደግሞ ተጻፈ።

"ሰሌዳቹን አየን። እነዚህ ነገሮች እውነት እንደሆኑ እንመሰክራለን። "



## የስምንት ሰዎች ምስክርነት

ይህንን መጽሐፍ ለምታዩ ለዓለም ብሔሮች ህዝቦች፣ጐሳዎችና ሁሉ ታናሹ ዬሴፍ ስሚዝ መጽሐፉን እንደተረጐመና በመጽሐፉም ውስጥ የተጠቀሱትን ሰሌዶች እንዳሳየን እንመሠክራለን።

ከወርቅ የተሠሩ ይመስላሉ የመጽሐፉ ትርጉም የተመሠረተባቸው ሰሌዶች በእጃችን ይዘናቸዋል። በላያቸው ላይ የተቀረፁትን ጽሑፎቹ አይተናል። ድሮ የተሠሩ ይመስላሉ። እንግዳ ነገሮች ይመስለሉ። ዬሴፍ ስሚዝ እነሱን እንዳሳየን በጽምና እንመሰክራለን።

ሰሌዶቹን አይተናል። አንስተናቸዋል። እነዚህ ሰሌዶች እንደነበሩን እናውቃለን። ሰሌዶቹን ስለ ማየታችን እግዚአብሔር ምስክራችን ነው አንዋሽም። ዓለም ሁሉና የዓለም ሕዝብ ያዩ ዘንድ ስማችን አንፈር ማለን።

ክርስቲያን ዊትመር
ያቆብ ዊትመር
ጴጥሮስ ዊትመር (ታናሹ)
ዮሐንስ ዊትመር
ሂራም ፔጅ
ዮሴፍ ስሚዝ (ታላቁ)
ሂሩም ስሚዝ
ሳሙኤል ስሚዝ

በኛ ላይ የአሮናዊ ክህነት የሰጠው መልዐክ የገባውን ቃል እንዲፈፅም በዚያ ጊዜ ጉጉ ነበርን። ታማኞች ከሆን የመልከጼዴቅ ክህነት እንደምንቀበል ነግሮን ነበር። ይህ ክህነት በሰው እራስ ላይ እጅ የማኖርና የቅዱስ መንፈስ ስጦታ የመስጠትን ሃይል ይጨምራል።

(ነቢዩም አለ። እርሱና ኦሊቨር ካውደሪ ከጴጥሮስ፣ከያዕቆብና ከዬሐንስ የመልከጼዴቅ ክህነት ሱስኩዊሃና በተባለ ወንዝ ዳርቻ በሃርሞኒና በኮልስቪል ከተማዎች መካካል ተቀብለዋል። ሃርሞኒ በፔንስልቫኒያ ውስጥ

"የመልከጼዴቅ ክህነት ከጴጥሮስ ከያዕቆብና ከዩሐንስ ተቀበሉ። "



የሚገኝ ሲሆን ኮልስቪል በንው ዬርክ ይገኛል። )

## ቤተክርስቲያን ተመሠረተ

የሞርሞን መጽሐፍ በመጻፍ ላይ እያለን ባገኘን ዕድል ሁሉ የሆነውን ነገር ለሌሎች እንነግር ነበር። ለአማኞችም ቤተክርስቲያን እንድናደራጅ መታዘዛችንን ነገርናቸው።

ቤተክርስቲያን ለመመሥረት በአቶ ጴጥሮስ ዊትመር (ታላቁ) ቤት ተሰበሰብን። ቀኑም ሚያዝያ 6 – 1830 ማክሰኞ ዕለት ነበር። ስብሰባችን ለሰማያዊ አባት በፀሎት መጸለይ ጀመርን። እንደታዘዝነውም እያንዳንዱ ሰው ስለእግዚአብሄር መንግሥት የምናስተምር አስተማሪዎች መሆናችንን ይቀበል እንደሆነ ጠየቅን።

በታዘዝነው መሠረት ቤተክርስቲያን በማቋቋማችን ይደሰቱ እንደሆነ ጠየቅናቸው። በመስማማት ድምፅ ሰጡ። ከዚያ በኋላ እጄን በኦሊቨር ካውደሪ እራስ ላይ አኖርኩና የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ካህን አድርጌ አፀናሁት። እርሱም እኔን የዚያው ቤተክርስቲያን ካህን አድርጦ አፀናኝ። ዳቦ ወስደን ባርከንና ቆርሰን ከእነርሱ ጋር በላን። ከዚያ በኋላ ወይን ወስደን ባረክነውና ከነርሱ ጋር ጠጣን።

ከዚያም በኋላ እዚያ በነበሩት ሁሉ ራስ ላይ እጃችንን አኑረን የቅዱስ መንፈስን ስጦታ ተቀብለው የፀኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክር ስቲያን አባል ይሆኑ ዘንድ ቅዱስ መንፈስም በታላቅ ሃይል ወደኛ መጣ። አንዳንዶቻችን ትንቢት ተናገረን። ሁላችም ጌታን አመስግነን እጅግ ተደሰተን።

ከዚያም ባኋላ መንፈስ በመራን መሠ ረት አንዳንድ ሰዎችን መርጠን በተላየዩ የክህነት ቢሮዎች አፀናናቸው። በእግዚአብ ሔር ፀጋ አማካይነት የተሰጠንን የቅዱስ መንፈስ ሃይልና በረከት እያየንና እየተሰማን

አስደሳች ጊዜ አሳለፍን። ስብሰባችን በመፍደም የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባሎች መሆናችንን ስላወቅን ተደሰትን። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናችን ስላወቀ ተደሰተን። በታዘዝነውና በኋለኛው ቀን በራዕይ በተገለፀልን መሠረትና በሐዲስ ኪዳን የቤተክርስቲያን አደረጃጀት መሠረት አደራ ጀነው።

አሁን ያነበብነው የዩሴፍ ስሚዝ ቀጥታ ምስክርነት ነው። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዲቋቋም ምክንያት የሆኑትን ይነግረናል። ወዲያው ቤተ ክርስቲያኑ ከተቋቋመ በኋላ እርሱና ተከታዩቹ ከኒው ዩርክ ስቴት በኦሃዩ ውስጥ ከርትላንድ ወደሚባል ከተማ ሄዱ።

እዚያም ውብ ቤተመቅደስ ሠርተው ብዙ ሰዎች ወንጌል ማስተማር ጀመሩ። የቤተክርስቲያናት አባሎች ቁጥር ቶሎ ጨመረ። በሚሱሪ ስቴት ውስጥ ብዙ ትምህ ርት ተሰጠ። በኋላም አብዛኛው የቤተክርስ ቲያን አባሎች ወደሚሱሪ ሄዱ።

በዚህ ጊዜ ሰዎች ሌሎች ሃይማኖቶችን ይነቀፉ ነበር። የሚሱሪ ሰዎች በኋለኛው ቀን ቅዱሳን አባሎች በጣም ተቆጥተው ከመሬታ ቸው አባረሩዋቸው። ከመሬታቸውና ከቤታ ቸው አስገድደው አባረሩዋቸው። እነርሱም እርሻቸውንና የሚያመልኩበትን ሥፍራ ትተው። ወደ ኢሌኖይ ስቴት ሄዱ። የዚያ ስቴት ሰዎች የኋለኛው ቀን ቅዱሳንን በደስታ ተቀብለው በችግራቸው አረዱዋቸው። ከዝያም ሰፊ ረግረግ ሥፍራ በሚሲሲፒ ወንዝ ዳርቻ ገዙ። ረግረጉን አስመጥጠው ናቩ (ውብ) የተባለ ከተማ ከተሙ።

(በዚያን ጊዜ በስቴቱ ትልቁ ከተማ ነበር። ) ሚሲዮናውያንና ከእንግሊዝ በመጡ ሰዎች ምክኒያት ትምህርት ስለተሰጠ የአባሎች ቁጥር በብዙ ጨመረ። ለጊዜው ከበሩ።

በናቩ ውስጥ ረጅም ሰላም አልተገ ኘም። ሌሎች ሰዎች የኋላኛው ቀን ቅዱሳንን ሃይማኖት ነቀፉ። አባሎቹን አሳደዱ። ዮሴፍ

ሰሚዝና ወንድሙ ሃይሩን በውሸት ተከሰው ታሠሩ። ባለሥልጣኖች እስረኞቹ ፍርድ በመጠበቅ ላይ ሳሉ መብታቸውን ለማስጠበቅ ዋስትና ሰጡ።

ቢሆንም ጥበቃ አላደረጉላቸውም። ሰኔ 27 ቀን 1844 ዓ·ም·ዮሴፍ ስሚዝና ሃይሩን ከርቴጅ ከተማ ውስጥ እሥር ቤት ሳሉ ፊታቸ ውን ቀለም በተቀቡ ሁከተኞች በጥይት ተመ ትተው ሞቱ።

ከዝያም ብሪጋም ያንግ የቤተክርስቲያን መሪና ነቢይ ሆነ። እርሱም የኋላኛው ቀን ቅዱሳንን ከኢሊኖይ ውጭ መርቶ አስወጣቸው። የሰሜን አሜሪካን ታላቅ ሜዳዎች አቋርጠው ወደ ምዕራብ ሮኪ ተራራዎች መራቸው። አካባቢው በረሃ ነበር። ሳይዘገይ ከበሩ። ዘሬ በብዙ አገር የሚገኙ በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ዮሴፍ ስሚዝን እንደእግዚአብሔር ነቢይ ይቀበሉታል። የኋላኛው ቀን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክር ስቲያን እርሱ በተቀበለው ራዕይ፣ባስተማረው ቅዱስ ትምህርትና በእርሱ አማካይነት በታደሰው የክህነት ሃይል የተመሠረተ ነው።

## የሚስዮን አድራሻዎች

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሚሲዮን ቢሮዎች ቀጥሎ ተጽፈዋል። ስለቤተክርስቲያኑና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እነዚህን ቢሮዎች በመጐብኘትና ወይም በመጻፍ ይበልጥ ለመማር ትችላለህ።


Missionary Department
The Church of Jesus Christ
of Latter-day Saints
50 East North Temple
Salt Lake City, Utah  84150

Area Office
The Church of Jesus Christ
of Latter-day Saints
751 Warwick Road
Solihull, West Midland, B91 3DQ
ENGLAND

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን

# የኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተክርስቲያን

AMHARIC

4 02326 67506 9

32667 506